جمعية خدمة المحتوى
الإسلامي باللغات

ضيوف الرحمن
hajjumrh.com



# የጉዞ ሰነሰርዓትና ህግጋቶቹ

ضيوف الرحمن
hajjumrh.com

شركاء التنفيذ :

دار الإسلام | بيان الإسلام | رواد التراجم | المحتوى الإسلامي

يتاح طباعة هذا الإصدار ونشره بأي وسيلة مع الالتزام بالإشارة إلى المصدر وعدم التغيير في النص

Tel : +966 50 244 7000
info@islamiccontent.org
Riyadh 13245-2836
www.islamiccontent.org

ምስጋና የአለማት ጌታ ለሆነው አላህ የተገባ ነው። ሶላትና ሰላም በነብያችን ሙሐመድ፣ በቤተሰቦቻቸውና በባልደረቦቻቸውም ላይ ሁሉ ይስፈን።

**በመቀጠልም፦**

ይህ የጉዞ ስነስርዓትና ህግጋትን በተመለከተ የሚያትት አጠር ያለ መልዕክት ነው። አንድ ተጓዥ አብዛኛው ጊዜ የሚያስፈልጉትን ጉዳዮች ለማብራራትም ጥረት አድርገናል።

ለተከበረው አላህ ብቻ ጥርት ተደርጎ የተዘጋጀና ለመላው ሙስሊሙ ማህበረሰብም ጠቃሚ እንዲያደርግልን አላህን እንጠይቀዋለን።

የእስላማዊ አስተምህሮቶችን በተለያዩ ቋንቋዎች አገልግሎት ማህበር የዕውቀት ዘርፍ ኮሚቴ

**የእስላማዊ አስተምህሮቶችን በተለያዩ ቋንቋዎች አገልግሎት ማህበር የዕውቀት ዘርፍ ኮሚቴ**

# የመጀመሪያው፡
# የጉዞ ስነስርዓት



ضيوف الرحمن
hajjumrh.com

# የመጀመሪያው: የጉዞ ስነስርዓት

ሐጅ ለማድረግ ወይም ለሌላ አምልኮዎች ጉዞ የሚያደርግ ሰው የሚከተሉት ነጥቦች ላይ ትኩረት ሊያደርግ ይገባል:

**ስለሚሄድበት ወቅት፣ መጓጓዣ፣ ስለሚያካሂደው ጓደኛ፣ ወዳሰበው ቦታ የሚወሰዱ በርካታ መንገዶች ካሉ ስለሚሄድበት የመንገድ አቅጣጫ (ሰግዶ) የላቀውን አላህን ያማክር፤**

- የእውቀትና የመልካም ባለቤት የሆኑን ሰዎችንም በዚህ ጉዳይ ያማክር፤
- የሐጅና ዑምራ ጉዞዎች ግን ቅዱስ ጉዞዎች ስለመሆናቸው ምንም ጥርጥር የለውም።
- አላህን የሚያማክርበት አፈፃፀሙም: ሁለት ረከዓ ይሰግዳል ቀጥሎ ከነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በርሳቸው ላይ ይሰፈንና) የመጣውን ዱዓ ያደርጋል።



# ማሰቡና ወደርሱ መቃረብን ማሰቡ ግዴታ ነው።,

እንዲሁም የዱንያን ሰባሪ ጥቅም ከማሰብ ወይም ፋከራን ከማሰብ ወይም ቅጥያ ስም ማግኘትን ከማሰብ ወይም ይዩልኝና ይሰሙልኝን ከማሰብ መጠንቀቅ ይገባዋል። ይህ ስራው እንዲበላሽና ተቀባይነት እንዲያጣ ከሚያደርጉ ምክንያቶች መካከል አንዱ ነውና።

**የላቀው አላህ እንዲህ ብሏል:**

> قُلْ إِنَّمَا أَنَا بَشَرٌ مِّثْلُكُمْ يُوحَىٰ إِلَيَّ أَنَّمَا إِلَٰهُكُمْ إِلَٰهٌ وَاحِدٌ فَمَن كَانَ يَرْجُو لِقَاءَ رَبِّهِ فَلْيَعْمَلْ عَمَلاً صَالِحًا وَلا يُشْرِكْ بِعِبَادَةِ رَبِّهِ أَحَدًا
>
> እኔ አምላካችሁ አንድ አምላክ ብቻ ነው ማለት ወደኔ የሚወረድልኝ ቢጤያችሁ ሰው ብቻ ነኝ። የጌታውንም መገናኘት የሚፈልግ ሰው፤ መልካም ሥራን ይሥራ። በጌታውም መገዛት አንድንም አያጋራ» በላቸው፡

## በሐዲሠል ቁድሲይም እንደተላለፈው፡

> **እኔ በሽርክና ከመጋራት ከተብቃቁ ሁሉ እጅግ የተብቃቃሁ ነኝ። ከኔ ጋር ሌላን አጋርቶ ስራን የሰራ እሱንም ማጋራቱንም እተወዋለሁ።**



ضيوف الرحمن
hajjumrh.com

## ወይም ክልክል የሆነበትን ነገር እንዳይፈፅም ከመጓዙ በፊት የዑምራና የሐጅን ህግጋትንና የጉዞ ህግጋትን መገንዘብ ይገባዋል።

ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በርሳቸው ላይ ይስፈንና) እንዲህ ብለዋል፦

**“አላህ መልካም ለሻለት ሰው ሃይማኖቱን ያስገነዝበዋል።”**

## የሐጅ ወይም የዑምራ ጉዞ የሚያደርግ ሰው ለሐጁና ዑምራው ሐላል የሆነ ገንዘብ መምረጥ አለበት።

ምክንያቱም አላህ መልካም ነው ከመልካም ውጪም አይቀበልም። በተጨማሪም ሐራም የሆነ ገንዘብ የዱዓን ተቀባይነት የሚያሳጣ አንዱ ምክንያት ነውና።

## ከሁሉም ወንጀሎችና ሐጢዓቶች ተውበት ማድረግ፤

ገንዘባዊም ሆኑ ክብር ነክ ወይም ከዛ ውጪ ባሉ ጉዳዮች ሰዎች ላይ የሰራው ግፍ ካለ መመለስና ይቅርታቸውን መጠየቅ ይኖርበታል።

## አንድ ጉዞ የሚወጣ ሰው፤

ሰው ዘንድ ያለውንም ሰው ላይ ያለበትንም ኑዛዜውን መጻፉ ይወደድለታል። ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በርሳቸው ላይ ይስፈንና) እንዲህ ብለዋል

**“አንድ ሙስሊም የሆነ ሰው አንዳች ሊናዘዘው የፈለገው ጉዳይ እያለ ኑዛዜው እርሱ ዘንድ ሳይጻፍ ሁለት ቀን ሊያድር አይገባውም።”**

ኑዛዜውንም በሰዎች ያስመሰክር፤ በርሱ ላይ ያሉበትን እዳዎችንም ይክፈል፤ እርሱ ዘንድ የተቀመጡ አደራዎችንም ወይ ለባለቤቶቻቸው ይመልስ ወይም ደሞ እርሱ ዘንድ እንዲቆይ ያስፈቅዳቸው።

**አንድ ጉዞ የሚወጣ ሰው ለጉዞው መልካም ጓደኛ መምረጡ ይወደድለታል። ጓደኛውን ሲመርጥም የሸሪዓ እውቀት ፈላጊ እንዲሆን ጥረት ያድርግ።**

ይህም ጉዞው ላይ፣ ሐጁ ላይና ዑምራው ላይ ለስህተት እንዳይጋለጥና መልካሙን እንዲገጠም ከሚያደርጉት ምክንያቶች መካከል አንዱ ነው። ይህም ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በርሳቸው ላይ ይስፈንና) እንዲህ ሰላሉ ነው

**"ሰውዬው በጓደኛው ሃይማኖት ላይ ነው። አንዳችሁ የሚጎዳኘውን ሰው ይመልከት።"**

ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በርሳቸው ላይ ይስፈንና) እንዲህም ብለዋል :

**"ከአማኝ በቀር አትጎዳኝ፤ አላህን ከሚፈራ ሰው በቀርም ምግብህን አይብላ።"**

## ተጓዥ የሆነ ሰው ቤተሰቡን፣ ቅርብ ዘመዶቹን፣ ጎረቤቶቹን፣ ባልደረቦቹን መሰናበት ይወደድለታል።

ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በርሳቸው ላይ ይስፈንና) እንዲህ ብለዋል:

**《ጉዞ መውጣት የፈለገ ሰው ትቷቸው ለሚሄዳቸው እንዲህ ይበል: "አስተውዲዑኩሙሏህ አለዚ ላተዲዑ ወዳኢዑህ"» [ትርጉሙም: እናንተን (እንዲጠብቃችሁ) አደራውን ለማያጠፋው አላህ አደራ እሰጠዋለሁ።》**

ከነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በርሳቸው ላይ ይስፈንና) ባልደረቦች መካከል አንዱ ጉዞ መውጣት በፈለገ ጊዜም እርሳቸው እንዲህ በማለት ይሰናበቱት ነበር:

**《አስተውዲዑሏሃ ዲነክ ወአማነተክ ወኸዋቲመ ዓመለክ» (ትርጉሙም: ሃይማኖትህን፣ እምነትህንና የስራህን ፍፃሜ ለአላህ አደራ እሰጠዋለሁ።》**

ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በርሳቸው ላይ ይስፈንና) ጉዞ ከሚወጡ ሰዎች መካከል ከርሳቸው ምክር ፈልጎ ለሚመጣ ሰው እንዲህ ይሉ ነበር:

**《ዘወደከሏሁ ተቅዋ ወገፈረ ዘንበክ ወየሰረ ለከ አል-ኸይረ ሐይሡ ማኩንተ» (ትርጉሙም: አላህ ፍራቻውን ያስሰንቅህ፣ ወንጀልህንም ይማርልህ፣ የትም ሆነህ መልካምን ያግራልህ።》**

ضيوف الرحمن
hajjumrh.com

አንድ ጉዞ መውጣት የፈለገ ሰውዬ ወደ ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በርሳቸው ላይ ይስፈንና) በመምጣት "የአላህ መልክተኛ ሆይ! ምከሩኝ" አለ፤ እርሳቸውም፡

«አላህን በመፍራትና በየሁሉም ከፍታ ላይ ስትወጣ" ተክቢራ (አላሁ አክበር) እንድትል እመክርሃለሁ።" አሉት። በሄደም ጊዜ "አላህ ሆይ! መሬትን ሰብስብለት (አሳጥርለት) ጉዞውንም አቅልልለት" አሉ።»

ጉዞ ሲወጣ ከራሱ ጋር ቃጭል፣ የሙዚቃ መሳሪያዎችና ውሻ አብሮ አይያዝ።

ይህም አቡ ሁረይራ (አላህ መልካም ስራቸውን ይውደድላቸውና) ባስተላለፉት ሐዲሥ የአላህ መልክተኛ (የአላህ ሶላትና ሰላም በርሳቸው ላይ ይስፈንና) እንዲህ ስላሉ ነው

«መላእክቶች ውሻም ይሁን ቃጭል) ያለበትን ጉዞ አይጎዳኙም።»



## ከአንድ በላይ ሚስቶች ኑረውት ለጉዞ አንዷን ብቻ ይዞ መውጣት ከፈለገ በመካከላቸው እጣ ይጥላል።,

እጣው የደረሳት ማንኛዋም ሚስቱ አብራው ወደ ጉዞው ትሄዳለች። ይህም ዓኢሻህ (አላህ መልካም ስራዋን ይውደድላትና) እንዲህ ስላለች ነው፡

**የአላህ መልክተኛ (የአላህ ሶላትና ሰላም በርሳቸው ላይ ይስፈንና) ጉዞ መውጣት የፈለጉ ጊዜ በባለቤቶቻቸው መካከል እጣ ይጥሉ ነበር። እጣ የደረሳት ማንኛዋም ባለቤታቸው ከርሳቸው ጋር አብራ ለጉዞ ትወጣ ነበር።**

## የሚቻል ከሆነ ሀሙስ እለት በቀኑ መጀመሪያ ላይ ለጉዞ መውጣት ይወደድለታል።,

ይህም ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በርሳቸው ላይ ይስፈንና) ስለፈፀሙት ነው። ከዕብ ቢን ማሊክ (አላህ መልካም ስራቸውን ይውደድላቸውና) እንዲህ አሉ፡

**የአላህ መልክተኛ (የአላህ ሶላትና ሰላም በርሳቸው ላይ ይስፈንና) ለጉዞ የወጡ ጊዜ ከሀሙስ ቀን ውጪ የሚወጡት በጣም ለጥቂት ጊዜያት ነበር።**

## ለጉዞም ይሁን ከዛ ውጪ ወደ ሆነ ቦታ ሲወጣ ከቤት ሲወጣ የሚባለውን ዱዓ ማድረግ ይወደድለታል፡

ሲወጣ እንዲህ ይላል: (ቢስሚላሂ ተወከልቱ ዐለላሂ፣ ወላ ሐውለ ወላቁወተ ኢላ ቢላህ፤ አልላሁመ ኢንኒ አዑዙ ቢከ አን አዲለ አው ኡደለ አው አዚለ አው ኡዘለ አው አዝሊመ አው ኡዝለመ አው አጅሀለ አው ዩጅሀለ ዐለየ) ትርጉሙም (በአላህ ስም በአላህ ላይ ተመክቼ እወጣለሁ። ኃይልም ይሁን ብልሃት በአላህ ፈቃድ ካልሆነ በቀር የለም። አላህ ሆይ! እኔ ከመጥመም ወይም ከማጥመም ወይም ወንጀል ላይ ከመውደቅ ወይም ሌላን ወንጀል ላይ ከመጣል ወይም ከመበደል ወይም ከመብበደል ወይም የመሃይማን ስራ ከመስራት ወይም የመሃይማን ስራ እኔ ላይ ከሚሰራብኝ ባንተ እጠበቃለሁ።) ማለት ነው።

## እንስሳውን ወይም መኪናውን ወይም ፕሌኑን ወይም ከዛ ውጪ ባሉ መሳፈሪያዎች ላይ ሲሳፈር እንዲህ;

ብሎ የጉዞን ዱዓ ማድረጉም ይወደድለታል

አላሁ አክበር አላሁ አክበር አላሁ አክበር ሱብሓነልለዚ ሰኽኸረ ለና ሀዛ ወማ ኩና ለሁ ሙቅሪኒን* ወኢና ኢላ ረቢና ለሙንቀሊቡን፤ አልላሁመ ኢንና ነስአሉከ ፊ ሰፈሪና ሀዛ አልቢርረ ወትተቅዋ፣ ወሚነል ዐመሊ ማ ተርዷ፣ አልላሁመ ሀውዊን ዐለይና ሰፈረና ሀዛ፣ ወጥዊ ዓ ዐና ቡዕደሁ፣ አልላሁምመ አንተስ -ሷሒቡ ፊ ሰፈር፣ ወልኸሊፈቱ ፊልአህል፣ አልላሁምመ ኢንኒ አዑዙ ቢከ ሚን ወዕሣኢ ሰፈር፣ ወከኣበቲል መንዘር፣ (123) ወሱኢል ሙንቀለብ ፊልማሊ ወልአህል

---

(1) 284/4) ወዕሣኢ-ስ-ሰፈር ማለት: የጉዞ መከራ ማለት ነው። አልኢፍሷሕ ዐን መዓኒ ሲሓሒ.
(2) (284/4) መጥፎ ገፅታ፣ በሀዘን የተጎሳቀለ ማንነት ማለት ነው። አልኢፍሷሕ ዐን መዓኒ ሲሓሕ
(3) 284/4) ማለት: መመለስ ማለት ነው። አልኢፍሷሕ ዐን መዓኒ ሲሓሕ (አልሙንቀለብ)

(ትርጉሙም: አላህ ታላቅ ነው። አላህ ታላቅ ነው። አላህ ታላቅ ነው። እኛ የማንችለው ሆነን ሳለ ይህንን ለኛ ያገራልን ጌታ ጥራት ይገባው። እኛ ወደ ጌታችን ተመላሾች ነን። አላህ ሆይ! እኛ በዚህ ጉዟችን በጎን ነገርና ፍራቻን፣ ከስራም የምትወደውን እንጠይቅሃለን። አላህ ሆይ ይህንን ጉዟችንን አቅልልልን፣ ርቀቱንም ስብስልን። አላህ ሆይ! እኛን በጉዟችን የምትጎዳኘን፣ በቤተሰቦቻችን ጉዳይም የምትተካን አንተው ነህ። አላህ ሆይ! እኔ ከጉዞ መከራ፣ መጥፎ በሆነ ገፅታ ከመታየትና ወደ ቤተሰቦቼና ንብረቶቼ መጥፎ አመላለስ ከመመለስ በአንተ እጠበቃለሁ።) ማለት ነው።



## ያለ ኣደኛ ብቻውን ባይጓዝ ይመረጣል።

ይህም ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በርሳቸው ላይ ይስፈንና) እንዲህ ስላሉ ነው፡

**“ሰዎች በብቸኛነት ምክንያት (የሚደርሰውን አደጋ) እኔ የማውቀውን ያህል ቢያውቁ ኖሮ አንድ በምሽት ብቻውን የሚጋልብ ሰውዬ (ብቻውን) አይጓዝም ነበር።”**

## ተጓዦቹ ከመካከላቸው አንዱን መሪያቸው ያድርጉ።

ይህም ህብረታቸውን የሚሰበስብ፣ ለስምምነት የሚጋብዝ ስለሆነና አላማቸውን ለማግኘት ስለሚያበረታ ነው።

ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በርሳቸው ላይ ይሰፈንና) እንዲህ ብለዋል፡

**« ሶስት ሰዎች ለጉዞ ከወጡ አንዱን መሪያቸው ያድርጉ »**



አላህ በርሱ ላይ ግዴታ ያደረገበትን እምልኮ ለመወጣት፣ ክልክሎችን ለመራቅ፣ የላቀ ስነምግባርን ለመላበስ፣ እገዛውንና እርዳታውን ለሚፈልግ ሰው ለማገዝ፣

እውቀትን ለሚፈልግ ሰው እውቀትን ለመስጠት መጣር አለበት። በገንዘቡም ቸር መሆን ይገባዋል። ገንዘቡን ለነፍሱ ጥቅምና ለወንድሞቹ ጥቅምና ፍላጎት ፈሰስ ማድረግ ይገባዋል።

መንገድ በወጣበት ያላሰበው ጉዳይ አጋጥሞት ነገሮች ሊወሳሰቡበት ስለሚችል የጉዞ በጀቱንና ስንቁን ማብዛት ይገባዋል።



እነዚህን ሁሉ ሲፈፅምም የሚለመድና የሚላመድ ሰው እንዲሆን ፊቱን ፈትቶ፣

ነፍሱ ተደስታና ጓደኞቹንም ደስተኛ ለማድረግ እየጣረ መፈፀም ይገባዋል።

**ከጓደኞቹ ለሚያጋጥመው ደረቅ ባህሪና የሃሳብ ተቃርኖ መታገስ ይገባዋል።**

በመካከላቸው እንዲከበርና በውስጣቸው እንዲልቅ መልካም በሆነ መንገድ ይግባባቸው።

**ተጓዦች አንድ ስፍራ ላይ እረፍት ሲወስዱ እርስ በርሳቸው ተጠጋግተው መቀመጥ ይወደድላቸዋል።**

የተወሰኑ ሶሓቦች አንድ አካባቢ ላይ ሲያርፉ ወደ ሸለቆዎችና ወደ ተራራ ስር ተበታትነው ያርፉ ነበር።

ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በርሳቸው ላይ ይስፈንና) እንዲህ አሏቸው፡

> **“ይህ ወደ ሸለቆና ወደ ተራራ ስር ተበታትናችሁ ማረፋችሁ ከሸይጧን ነው።”**

ከዛን ጊዜ በኋላ ልብስ ቢዘረጋላቸው ሁሉንም በቅቷቸው በሚያስቀምጥ ደረጃ እርስ በርሳቸው ተጠጋግተው ይቀመጡ ነበር።



## ከጉዞም ይሁን ከሌላ ቦታ ወደ አንድ ሰፍራ በሚያርፍ ወቅት ከነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በርሳቸው ላይ ይስፈንና) ተረጋግጦ የመጣውን ዱዓ ማድረግ ይወደድለታል:

« አዑዙ ቢከሊማቲላሂ) አትታማት ሚን ሸሪ ማ ትርጉሙም (ኸለቅ (ሙሉ በሆነው የአላህ ንግግር ከፈጠረው ጎጂ ነገሮች እጠበቃለሁ።) ማለት ነው። »

እርሱ ይህንን ካለ ከዛ ሰፍራ ለቆ እስኪንቀሳቀስ ድረስ ምንም ጉዳት አያገጥመውም።

## ከፍ ወዳሉ ቦታዎች ላይ ሲወጣ ተክቢራ ማለት፣ ዝቅ ወዳሉ ሰፍራዎችና ወደ ሸለቆ ሲወርድ ደግሞ ተስቢሕ ማለት ይወደድለታል። ጃቢር (አላህ መልካም ስራውን ይውደድለትና) እንዲህ ብሏል፦

«ከፍ ወዳሉ ቦታዎች ስንወጣ ተክቢራ፣ ስንወርድ ተሰቢሕ እንል ነበር። »

ተክቢር በሚሉበት ወቅትም ድምፅን ከፍ ማድረግ አይገባም። ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በርሳቸው ላይ ይስፈንና) እንዲህ ብለዋል

**እናንተ ሰዎች ሆይ! ለነፍሳችሁ እዘኑ።) እናንተ ደንቆሮና ሩቅ የሆነን ጌታ አይደለም'ኮ የምትጣሩት። እርሱ ከናንተ ጋር ነው። እርሱ ሰሚና ቅርብ ነው።**


## የጉዞ ወቅቱን ምሽት ላይ በተለይ በምሽቱ መጀመሪያ ላይ ቢያደርግ ይወደድለታል። ይህም ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በርሳቸው ላይ ይስፈንና) እንዲህ ስላሉ ነው:

**የምሽት ጉዞን አደራ ተጓዙ። ምድር በምሽት ትሰበሰባለችና።**

ضيوف الرحمن
hajjumrh.com

# በጉዞ ወቅት ዱዓ ማብዛት ይወደድለታል።

ይህም ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በርሳቸው ላይ ይሰፈንና) እንዲህ ስላሉ ነው -፡



《ሶስት ዱዓዎች ተቀባይነት አላቸው። ተቀባይነት ለማግኘታቸውም ምንም ጥርጥር የለውም። የተበዳይ ዱዓ፣ ጉዞ ላይ ያለ ሰው የሚያደርገው ዱዓና ወላጅ ለልጁ የሚያደርገው ዱዓ ናቸው። 》

# ሁለተኛ: የጠሀራ አፈፃፀም በጉዞ ወቅት

## ጉዞ ላይ ያለ ሰው ለጠሃራው ትኩረት መስጠት ግዴታው ነው።

ትንሹ ሐደሥ ሲያጋጥመው ዉዱእ ያድርግ ጀናባ ሲያጋጥመው ደግሞ ገላውን ይታጠብ።

## ውሃ ካላገኘ ወይም ያለው

ውሃ ለመብሉና ለመጠጡ የሚፈልገው ያህል ትንሽ ውሃ ብቻ ከሆነ ተየሙም ያድርግ።



የ ተ የ ሙ ም አፈፃፀም: በሁለት እጆቹ መሬቱን ይመታ እና በነርሱ ፊቱንና መዳፎቹን ያብሳል።

## የተየሙም ጦሃራ ጊዜያዊ ጦሃራ ነው።

## ልክ ውሃ እንዳገኘ የተየሙሙ ጠሃራ ይበላሽና ውሃውን መጠቀሙ ግዴታው ይሆናል።

ጀናባ አጋጥሞት ተየሙም ካደረገ በኋላ ከዚያም ውሃ ቢያገኝ ገላውን ታጥቦ ጀናባውን ማንሳት ግዴታው ይሆናል።

ضيوف الرحمن
hajjumrh.com

ተፀዳድቶ ተየሙም ቢያደርግ እና ከዚያም ውሃ ቢያገኝ ዉዱእ ማድረግ ግዴታው ይሆናል።

በሐዲሥ እንዲህ የሚል ተዘግቧል፡

> «አንድ ሙስሊም ለአስር አመት ውሃ ባያገኝ እንኳ ንፁህ አፈር የሙስሊም ዉዱእ ማድረጊያ (ሆኖ የሚቆጠር) ነው። ውሃ ያገኘ ጊዜ ግን አላህን ይፍራ! ሰውነቱንም ውሃ ያስነካ።»

**በሁለት ኹፎች ላይ ማበስ በቁርአን፣** በሐዲሥና በአህሉ ሱና ዑለሞች ስምምነት ባጠቃላይ የተደነገገ ነው።

**በሁለት ኹፎች ላይና በነርሱ ተመሳሳይ ብይን ያለው ነገር ላይ ለማበስ የሚከተሉት መስፈርቶች መሟላት አለባቸው**

- ኹፎቹ ወይም ካልሲዎቹ ንፁህ መሆን አለባቸው፤
- ዉዱእ ያለው ሆኖ ሊለብሳቸው ይገባል፤
- ኹፎቹ ዉዱእ ሲያደርግ የግዴታ ማጠብ የሚገባውን የእግር ክፍል የሚሸፍኑ መሆን አለበት፤



**የሚያብሰው ትንሹ ሐደሥ ሲያጋጥመው ብቻ መሆን አለበት። ጀናባን ወይም ገላ መታጠብን የሚያስገድዱ ነገሮች ሲያጋጥሙት ኹፋ ላይ ማበስ አይፈቀድለትም።**

የሚያብሰውም በሸሪዓ በተገደበለት ወቅት ውስጥ መሆን አለበት። እርሱም ሀገሩ ተቀማጭ ለሆነ ሰው አንድ ቀን ከነሌሊቱ ሲሆን ጉዞ ላይ ላለ ሰው ደግሞ ሶስት ቀን ከነሌሊቱ ነው። ይህ የጊዜ ገደብ የሚጀምረውም በትክክለኛው የዑለሞች አቋም መሰረት ዉዱእ ካጠፋ በኋላ መጀመሪያ ማበስ ከጀመረበት ጊዜ ጀምሮ ሀገሩ ተቀማጭ የሆነ ሰው ልክ በሃያ አራተኛ ሰአቱ ጊዜ ገደቡ ሲጠናቀቅበት ጉዞ ላይ ያለ ሰው ደግሞ ልክ በሰባ ሁለተኛ ሰአቱ ይጠናቀቅበታል።



ضيوف الرحمن
hajjumrh.com

# የማበስ ፍቃዱ ከሶስት ነገሮች መካከል አንዱ ከተከሰተ ይበላሻል:

- ጀናባን የመሰለ ገላ መታጠብ የሚያሰገድድ ነገር ከተከሰተ የግድ መታጠብ ስላለበት የማበስ ፍቃዱ ይበላሻል።
- ካበሰ በኋላ ካወለቃቸው፤
- በሸሪዓ የተገደበው የጊዜ ገደብ ከተጠናቀቀም የማበስ ፍቃዱ ይበላሻል።

* * *



# ጉዞ ላይ ሶላትን የማሳጠር ህግጋት

## ጉዞ ላይ ሞልቶ ከመስገድ ይልቅ አሳጥሮ መስገድ በላጭ ነው።

ነገር ግን ጉዞ ላይ ያለ ሰው ባለ አራት ረከዓ ሶላቶችን አራት ረከዓ አድርጎ ሞልቶ ቢሰግድ ሶላቱ ትክክለኛ ናት። ይሁን እንጂ በላጭ የሆነውን ተቃርኗል።

## ጉዞ ላይ ያለ ሰው በሚኖርበት መንደር ወይም ከተማ ካሉ አጠቃላይ ቤቶች አልፎ ሲወጣ ማሳጠር ይችላል።

ጉዞ ላይ ያለ ሰው በሚኖርበት መንደር ወይም ከተማ ካሉ አጠቃላይ ቤቶች አልፎ ሲወጣ ማሳጠር ይችላል።



ضيوف الرحمن
hajjumrh.com

## የሶላት ወቅት ከገባ በኋላ ቢጓዝ ወቅቱ ከመውጣቱ በፊት ስለሆነ ጉዞ የጀመረው ማሳጠር ይችላል።

## ጉዞ ላይ ያለ ሰው በሚያስፈልገው ወቅት

**በዝሁርና በዐስር መካከል፣**

**በ መ ግ ሪ ብ ና በዒሻ**

መካከል ሰብስቦ መስገዱ ሱና ነው።

ጉዞውን ሳያርፍ እየገሰገሰ ከቀጠለ አስቀድሞ ወይም አዘግይቶ ለርሱ ምቹ በሆነው ወቅት ሰብስቦ ይሰግዳል።



## ሰብሰቦ መስገዱ ጉዞ ላይ ላለው ሰው አስፈላጊ ካልሆነ በቀር (በየወቅቱ ነጣጥሎ እንጂ) ሰብሰቦ አይስገድ።

ለምሳሌ አንድ ሰፍራ ላይ አርፎ የሁለተኛው ሶላት ወቅት ከገባ በኋላ እንጂ መንቀሳቀስ በማይፈልግበት ሁኔታ ላይ ከሆነ በላጩ ሰብሰቦ አለመስገዱ ነው። ምክንያቱ ደግሞ መሰብሰቡ ምንም ስለማያስፈልገው ነው። ለዛም ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በርሳቸው ላይ ይስፈንና) በመሰናበቻ ሐጅ ወቅት ሚና ባረፉ ጊዜ ስላላስፈለጋቸው ሰብሰበው አልሰገዱም።

## ሱና ሶላቶችን በተመለከተ

ጉዞ ላይ ያለ ሰው ሀገሩ የተቀመጠ ሰው የሚሰግደውን ሱና ሶላቶች ይሰግዳል። የዱሓ ሶላትን፣ የለይልና የዊትር ሶላትን ሌሎችንም ከዝሁር፣ ከመግሪብና ከዒሻ ቀብሊ,ያና ባዕዲ,ያ ሶላት ውጪ ያሉ ሱና ሶላቶችን መስገድ ይችላል። ከፈጅር ቀብሊ,ያ ውጪ ያሉ ቀብሊ,ያና በዕዲ,ያ ሶላቶችን ግን ሱናው አለመስገዱ ነው።

## ጉዞ ላይ እንደፕሌን፣ መኪና፣ መርከብና ሌሎችም መጓጓዣዎች ላይ ሱና ሶላቶችን መስገድ ይፈቀዳል።

ግዴታ ሶላት ከሆነ ግን ከአቅሙ በላይ እስካልሆነ ድረስ የግድ መውረድ ይኖርበታል።



## ጉዞ ላይ የሆነ ሰው ሀገሩ ተቀማጭ ከሆነ ሰው ኋላ መስገዱ ይበቃለታል።

ነገር ግን ጉዞ ላይ ያለው ሰው ከኢማሙ ጋር አብሮ ለመስገድ ያገኘው ሁሉንም ረከዓ ይሁን ወይም አንድ ረከዓና ከዛ በታች ቢሆንም ኢማሙ የመጨረሻው ተሸሁድ ላይ እያለ ከማስላመቱ በፊት ቢጀምር እንኳ ልክ እንደ ኢማሙ ሶላቱን ሞልቶ ነው የሚሰግደው። ከዑለሞች ሁለት የተለያዩ አቋሞች መካከል ትክክለኛውና ሚዛን የሚደፋው ይሄ ነው።

## አራተኛ: ከሐጅ፣ ከዑምራ ወይም ከጉዞ የመመለስ ስነስርዓት

ለመመለስ መፍጠን ይገባዋል። ያለአስፈላጊ ጉዳይ ጉዞ ላይ መቆየት አይገባውም።

ይህም ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በርሳቸው ላይ ይሰፈንና) እንዲህ ስላሉ ነው -

(ጉዞ የቅጣት ቁራጭ ነው። አንዳችሁን ምግቡን፣ መጠጡንና እንቅልፉን ይከለክለዋል። አንዳችሁ ጉዳዩን እንዳጠናቀቀ በፈጠነ ወደ ቤተሰቡ ይመለስ። )

ወደ ሃገሩ መመለስ በፈለገ ጊዜ መጓጓዣው ላይ እንደወጣ የጉዞን ዱዓ ይቅራና ይህንን ይጨምርበት

አዪቡን፣ ታኢቡነ፣ ዐቢዱነ) ትርጉሙም (ሊረቢና ሓሚዱን (ተመላሾች ነን፣ ተፀፃቾች ነን፣ ጌታችንን አምላኪዎችና አመስጋኞች ነን።

ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በርሳቸው ላይ ይስፈንና) ከጉዞ በሚመለሱ ወቅት እንደሚሉ የተረጋገጠውን ውዳሴ ከጉዞ በሚመለስ ወቅት ማለቱ ይወደዳል። እርሳቸው ከዘመቻ ወይም ከሐጅ ወይም ከዑምራ በሚመለሱ ወቅት ከፍ ያለ ቦታ ላይ በወጡ ቁጥር ሶስት ጊዜ ተክቢራ ይሉ እና

## ቀጥለው እንዲህ ይሉ ነበር፡

(ላኢላሃ ኢለሏሁ ወሕደሁ ላ ሸሪከ ለሁ፣) ለሁልሙልኩ፣ ወለሁል ሐምዱ፣ ወሁወ ዐላ ኩሊ ሸይኢን ቀዲር፣ አዩቡነ ታኢቡነ ዐቢዱነ ሳጂዱነ ሊረቢና ሓሚዱን፣ ሰደቀሏሁ ወዕደህ፣ (ወነሰረ ዐብደህ፣ ወሀዘመል አሕዛበ ወሕደህ ትርጉሙም (ከአላህ በቀር በእውነት የሚመለክ የለም፤ ብቸኛና አጋር የለውም። ንግስና ለርሱ የተገባ ነው። ምስጋናም ለርሱ የተገባ ነው። እርሱም በሁሉም ነገር ላይ ቻይ ነው። ተመላሾች፣ ተፀፃቾች፣ አምላኪዎች፣ ሰጋጆች፣ ለጌታችን አመስጋኞች ነን። አላህ ቃሉን በእውነት ሞላ፣ ባሪያውንም ረዳ፣ የጥመት ጭፍራንም ብቻውን አሸነፈ።)



## ሀገሩን በሚመለከትበት ወቅት፡

**( አዩቡነ፣ ታኢቡነ፣ ዐቢዱነ፣ ሊረቢና ሓሚዱን )**

ማለቱ ይወደድለታል። ይህንንም ሀገሩ እስኪገባ ድረስ ይደጋግመው። ይህንንም የሚያደርገው ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በርሳቸው ላይ ይስፈንና) ስለፈፀሙት ነው።

**ከቤተሰቡ ለረጅም ጊዜያት ርቆ ሲመለስ አስፈላጊ ሁኖ ወይም በምሽት እንደሚደርስ ቀድሞ አሳውቋቸው ካልሆነ በቀር በምሽት አይግባ።**

ይህም ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በርሳቸው ላይ ይስፈንና) ስለከለከሉ ነው። ጃቢር ቢን ዐብደላህ (አላህ መልካም ስራቸውን ይውደድላቸውና) እንዲህ አሉ

**(ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በርሳቸው ላይ ይስፈንና) ሰውዬው ወደ ቤተሰቡ በምሽት መግባቱን ከለከሉ። )**

የዚህንም ጥበብ ሌላኛው ዘገባ እንዲህ በሚል አብራርቶታል፡

**(ፀጉሯ ቅባት ሳይነካው ከርሞ የተንጨባረረባት እንድታበጥር፣ ባሏ ርቆ የከረመባት (የብልቷን ፀጉር) እንድትላጭ )** [4]

(4) ሽዕሣ) ማለት ፀጉሯ ቅባትና መበጠርን ካየ ጊዜያትን ያስቆጠረች ማለት ነው። (ኢስቲሕዳድ) ማለት ስለትን ለመላጨት መጠቀም ማለት ነው። (ሙገየባህ) ማለት ባሏ ከርሷ የራቀ ማለት 292 ነው። አትተሕሪር ፊ ሽርሒ ሶሒሕ ሙስሊም - አልአስበሃኒይ ( ገጽ

# በሌላ ዘገባ ደግሞ ፡

(የአላህ መልክተኛ (የአላህ ሶላትና ሰላም በርሳቸው ላይ ይሰፈንና) ሰውዬው ሚስቱ እየከዳችው መሆኑን ጠርጥሮ ወይም ነውሯን ለመሰለል አስቦ ወደ ቤተሰቡ በምሽት መግባቱን ከለከሉ። )

ከጉዞ ወደ ሃገሩ የሚገባ ሰው በቅድሚያ ቤቱ አካባቢ የሚገኝ መስጂድ በመግባት ሁለት ረከዐ ይሰገድ። ይህም ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በርሳቸው ላይ ይሰፈንና) ስለፈፀሙት ነው።



## አንድ ጉዞ የወጣ ሰው ከጉዞው ሲመለስ የራሱና የጎረቤቱ ልጆች አቀባበል ሲያደርጉለት እዝነት ሊያሳያቸውና በጎ ነገር ለነርሱ ማድረጉ ይወደድለታል።

ከኢብኑ ዐባስ (አላህ መልካም ስራቸውን ይውደድላቸውና) እንደተላለፈው እንዲህ አለ: «ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በርሳቸው ላይ ይስፈንና) መካ የገቡ ጊዜ የበኒ ዐብዱል ሙጦሊብ ህፃናቶች አቀባበል አደረጉላቸው። ከህፃናቶቹ መካከልም አንዱን ከፊታቸው አንዱን ከኋላቸው ተሸከሙ።» ዐብደላህ ቢን ጀዕፈር (አላህ መልካም ስራቸውን ይውደድላቸውና) እንዲህ አሉ :

(ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በርሳቸው ላይ ይስፈንና) ከጉዞ ሲገቡ እኛን ያገኙናል። እኔንና ሐሰንን ወይም ሑሰይንን ሲያገኙን መዲና እስኪገቡ ድረስ አንዳችንን ከፊት አንዳችንን ከኋላ ይሸከሙን ነበር። )

## ስጦታ መስጣጠት ልብን ስለሚያፋቅር፣ መቃቃርን ስለሚያስወግድ ይወደዳል።

መቀበሉና የስጦታውን ውለታ መመለስም ይወደዳል። ስጦታውን ከመቀበል የሚከለክለው ሸሪዓዊ ምክንያት እስከሌለ ድረስ ስጦታውን መመለስ ይጠላል። ለዚህም ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በርሳቸው ላይ ይስፈንና) እንዲህ ብለዋል

(ስጦታ ተሰጣጡ ትዋደዳላችሁ።)

ስጦታ መስጣጠት በሙስሊሞች መካከል ውዴታን ከሚያመጡ ምክንያቶች መካከል አንዱ ነው።

ضيوف الرحمن
hajjumrh.com



## አንድ ጉዞ የወጣ ሰው ወደ ሃገሩ የገባ ጊዜ በመተቃቀፍ ሰላምታ መለዋወጡ ይወደድለታል።

ይህም ከነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በርሳቸው ላይ ይሰፈንና) ባልደረቦች የተረጋገጠ ጉዳይ ነው። አነሰ (አላህ መልካም ስራውን ይውደድለትና) እንዲህ አለ

(በሚገናኙበት ወቅት በመጨባበጥ ሰላምታ ይለዋወጡ ነበር። ከጉዞ የገቡ ጊዜ ግን በመተቃቀፍ ነበር ሰላምታ የሚለዋወጡት።)

# تعرف على الإسلام

# بأكثر من 100 لغة

موسوعة القرآن الكريم
QuranEnc.com

ترجمات متقنة لمعاني القرآن الكريم بأكثر من (75) لغة

بيان الإسلام
byenah.com

مواد منتقاة للتعريف بالإسلام وتعليمه بأكثر من (120) لغة

موسوعة الأحاديث النبوية
HadeethEnc.com

ترجمات متقنة للأحاديث النبوية وشروحها بأكثر من (60) لغة

ضيوف الرحمن
hajjumrh.com

مواد منتقاة للحجـــاج والمعتمرين و الزوار بلغات العالم

جامع المحتوى الإسلامي باللغات
islamcontent.com

مواد إسلامية متنوعة وشاملة بأكثر من (125) لغة

موسوعات وخدمات إسلامية باللغات
s.islamenc.com

للمزيد من المواقع الإسلامية بلغـــات العـــالم

ضيوف الرحمن
hajjumrh.com

جمعية خدمة المحتوى الإسلامي باللغات